# ማስታወሻ

- ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) ቦርድ አባላት በያሉበት፤
- ከከፋለ ማሞ አለሜ*

መስከረም 12 ቀን 2004 ዓ.ም. (23 Sept. 2011)

**ጉዳዩ፡-** <u>በአምስተርዳም የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) ቢሮ ውስጥ ከገጠሙኝ የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች ህሊና ለጓሚና አዋራጅ ድርጊቶች እንዲሁም ካገጠጠው የሙስና አካባቢ ራስን ስለማግለል፡</u>

የኢትዮጵያን ህዝብ ተደራሽ አድርጎ ዜና፣ መረጃና ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን በሳተላይት በቀጥታ የሚያስራጨው ኢሳት በኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበር (ኢነጋማ) አባላትና ጉዳዩ በሚመለከታቸው በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሃይላት አማካኝነት በኔዘርላንድ መዲና አምስተርዳም ውስጥ ከዓመት በፊት መቋቋሙ ይታወሳል።

ይሁንና በኔዘርላንድ ኢሳት ቢሮ ከሙያ ስነምግባር ይልቅ፣ የአጎብዳጅነትና የሙሰኝነት ባህሪ እንዲሁም ማን አለብኝነትና፣ ከበላይ አካል ተወዳጅነትን ለማትረፍ ሲባል የፓርቲ ፖለቲካን የማስቀደም አባዜ አዝማሚያ ከዕለት ወደ ዕለት እያየለ መምጣት በነፃ ጋዜጠኝነት ላይ አሉታዊ ጫና ሊፈጠር ችሏል።

እናም ችግሩ ከእለት ወደዕለት ቢብስ እንጂ ሊሻሻል ባለመቻሉ እኔ ከፋለ ማሞ አለሜ ከትናንት ሐሙስ መስከረም 11 ቀን 2004ዓ.ም አንስቶ ከኢሳት የስራ መደቤ ለመሰናበት መገደዴን በአክብሮት እገልፃለሁ።

ከኢሳት የለቀቅሁበት ዓቢይ ምክንያት ድርጅቱ የተቋቋመበትን ዓላማና ግብ ሆን ብሎ ክፉኛ በማንጋደድ፤ የጠባብ ቡድን ፣ የዘመድ አዝማድ፣ የቤተሰብ መገልገያና በጋዜጠኝነት ሙያቸው ብቃት ሳይሆን በድርጅት ታማኝ አባልነታቸው በሚመኩ ግለሰቦች ከራስ ጠጉር እስከ እግር ጥፍሩ ተሞልቶ በዚሁ ሳቢያ የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ታሪክ እየጎደፈ በመምጣቱ ነው።

ከእነዚሁ የነፃው ፕሬስ ጋዜኞች ስነ-ምግባራትና ታሪክ እጅግ አጉዳፊ ከሆኑት፣ ከአምስተርዳሙ የኢሳት ቢሮ ላይ ጥንብ እንዳዩ አሞራዎች ከሚያንዧብቡት ጥቅም አሳዳጆች መካከል በዋነኛነት አወሳላችነቱ፣ ሌሎችንም በሙስና ጎዳና አሰማሪነቱና የድርጅት ንብረት አባካኝነቱ ጉልህ የጥፋት ሚና በሚጫወተው ግለሰብ ሃላፊ ላይ ለይቼ አተኩራለሁ።

በዚህ በትናንትናው ዕልት ማለትም በሐሙስ መስከረም 12 ቀን 2004 ዓ.ም ማስታወሿዬ ከዓመት በላይ የታዘብኩትን የጠባብ ቡድን አባላት ትስስር እና የቡድን የገንዘብ አከፋፈልን በመሳሰለው ረገድ በባለሙያ ግለሰቦች ላይ የሚፈጽመውን ተጽዕኖ ብሎም የቡድኑን አገልጋይ እየሆነ ከነፃው ፕሬስ ዘላቂ የሙያ ስነ-ምግባራት ጋር ባይተዋር የመሆንን ጉዞ እና የማይታረም ዝንባሌ ለማሳወቅ እሻለሁ።

የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበር (ኢነጋማ) ከተመሰረተበት ከመጋቢት 3 ቀን 1985 ዓ.ም አንስቶ ግልጽና የማያሰልስ ጥረቱ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎችን ዓላማ ግብ ማስመታት ነው። ይሄውም የሰፊውን የኢትዮጵያ ህዝብ ፖለቲካዊ ሃይል ወደፊት ተመልካችና ዘላቂ በሆነ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ላይ ማነጽና ያም ስርዓት የመጨረሻ ከፍተኛ ስልጣኑን በነፃ ህሊና ከሚካሄድ የምልዓት ህዝቡ ምርጫ የሚላበስ የሕዝቡ ወኪል መንግስት እንዲሆን ለማብቃት ነው።

የኢነጋማ ድርጅታዊ ትግል ከመጋቢት 3 ቀን 1989 ዓ.ም ወዲህ በተለይ ከአምባው የቀጠለው የዓለማቀፍ ኮሚቴው ትግል ሲሆን ይሄው በርከት ያሉ ብርቱ የአመራር አባላቱ በአንድነትና በአጋጣሚ ሊገናኙ ከቻሉበት ከኔዘርላንድ ያለማሰለስ በልዩ ልዩ ገጽታዎች የቀጠለው ትግል ነው። የኔዘርላንዱ የኢነጋማ ዓለም አቀፍ ኮሚቴ ትግሉን የቀጠለው በስደት ላይ ከነበረው የኢነጋማ ፕሬዝደንት እና የትግልና የሙያ ጓዶቹ ጋር በአዲስ አካባቢ በአዲስ የኢነጋማ ዓለም አቀፍ ኮሚቴ በታህሳስ 5 ቀን 1990 ዓ.ም አምስተርዳም ውስጥ ተዋቅሮ በመቋቋም ነው።

የኢነጋማ ዓለም አቀፍ ኮሚቴ አባላት ዓቢይ ዓላማ በአዲስ አበባ መዲና በዋናው የኢነጋማ ጽ/ቤትና በማህበሩ አመራር ላይ ከወደቀው የአፈና ቀንበር ለጊዜው መራቅና ከዓለም አቀፍ የፕሬስ ነፃነት ደጋፊዎችና ከሰብዓዊ መብት ጠባቂ ሃይላት ጋር በቅንጅት በመታገል ለኢትዮጵያ የተሻለ ዲሞክራሲያዊ ጎህ እንዲቀድ ማስቻል ነው።

በዚህ ረገድ ኢነጋማ ዓለምአቀፍ ኮሚቴ ለሐገር ቤቱ የኢነጋማ አመራር አጋር በመሆን ማህበሩ የህወሃት ወያኔን ተጽዕኖ በመቋቋም የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበር (ኢነጋማ) ድርጅታዊ ሃላፊነቱን በአስመስጋኝና በአሸላሚነት የብቃት ደረጃ እንዲወጣ ለማስቻል ከፍተኛ የትግል ድርሻውን አበርክቷል። እያበረከተም ነው።

ስለሆነም የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበር(ኢነጋማ) በኢትዮጵያ ውስጥ እያለና በኋላም በመለስ ዜናዊ መንግስት የተቀነባበረ ሴራ ከሐገር እንደወጣ እንዲቀር ሲደረግ ህይወቱ ህያው ሆኖ በትግሉ እንዲቀጥል ለማስቻል በተለይም በአምስተርዳም መዲና ከዘጠኝ ዓመታት በላይ ሳምንታዊ የአንድ ሰዓት ሁሉን አቀፍ የቴሌቪዥን ፕሮግራም በአማርኛ በማቅረብና በመጨረሻም የኢትዮ-ዳች ጋዜጠኞች ዓለም አቀፍ ጉባኤ የተሰኘ የማጠቃለያ ሴሚናር በሰኔ ወር 1998 ዓ.ም አምስተርዳም ውስጥ በማካሄድ የትግሉን አቅጣጫ በአዲስ መንፈስ ለመንደፍ በቅቶ እንደነበር ይታወሳል።

የኢነጋማ ሊቀ-መንበር ጋዜጠኛ ክፍሌ ሙላት እና የዓለም አቀፍ የጋዜጠኞች ፌዴሬሽን የአፍሪካ ቢሮ ሃላፊ እንዲሁም የሌሎች አጋር የጋዜጠኞች ማህበራት መሪዎችና የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ጥበቃ ድርጅቶች ተወካዮች በተለይም ስመ-ጥሩውና ጀግናው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር(ኢመማ) ፕሬዝደንት ዶ/ር ታዬ ወልደሰማዕት የተሳተፉበት ይህ የሁለት ቀናት ሴሚናር ካስተላለፋቸው የጋራ ውሳኔዎች መካከል አንኳሩ መደምደሚያ "ኢትዮጵያ በተነጠቀችው የነፃ ፕሬስ ቦታ አማራጭ ነፃ የመገናኛ ብዙሃን እንዲተከልና የነፃውን ፕሬስ ሙሉ አገልግሎት እንድታገኝ ማብቃት" የሚለው አኩሪ ነጥብ ይገኝ ነበር።

ይህንን ከማንኛውም ግፊት ነፃ የሆነ "አማራጭ" የመገናኛ ብዙሃን ከወያኔ ህወሃት በትር ፍጹም በራቀና ደህንነቱ በአስተማማኝ ደረጃ በሚጠበቅበት በአውሮፓ በተለይም ጠንካራ የኢነጋማ ቡድን በሰፈረበት በአምስተርዳም መዲና የማቋቋም ተገቢነቱ በአባላቱ በዕውን ታመነበት። በመሆኑም

የኔዘርላንዱ የኢነጋማ ቡድን አማራጭ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ማዕከል የማቋቋም ሃላፊነቱን ተቀበለ።

የኢነጋማ ዓለም አቀፍ ኮሚቴ በምኞት ደረጃ  ጥርት ብሎ በወጣው አማራጭ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን አደረጃጀት ላይ ከማንኛውም በወቅቱ ከነበሩት የኢነጋማ ስብስቦች መካከል የተሻለ ድርጅታዊ ህልውና ስለነበረውና ታሪኩም እንደሚመሰክረው ሁሉ ለጊዜው ባዶ የነበረውን የእናት ማህበሩን የኢነጋማን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ቦታ በመሙላት ቀጣዩን ተግባራት የማከናወን ሃላፊነት ወሰደ።

ይህ ዕውነታ የተደረሰው በሰኔ 3 እና 4 ቀናት 1998 ዓ.ም የሁለት ቀናት ሴሚናር መደምደሚያ ላይ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ወደ አምስት ዓመት ዕድሜ ማስቆጠሩ ይታወቃል። የአምስተርዳሙ የኢነጋማ የኢትዮ-ዳች ዓለም አቀፍ ጉባኤ (ሴሚናር) በሰኔ 3 እና 4 ቀናት 1998 ዓ.ም ከተካሄደ በኋላ በአሜሪካ ሒውስተን ቴክሳስ በሚገኘው የኢነጋማ ፕሬዝደደንት በጋዜጠኛ ክፍሌ ሙላት ሙሉ ዕውቅና እና ስምምነት የአምስተርዳሙ ጉባዔ የተቀበለው መመሪያና የስራ ሃላፊነት ወደፊት እንዲራመድ ተደርጓል። የአምስተርዳሙን ጉባዔ መመሪያ ለማስፈጸም የተወሰደውና የቀጠለው አንዱ ተከታታይ እርምጃ ህዝብ ግንኙነት እና የማስታወቂያ መኮንኑ በጋዜጠኛ ክንፉ አሰፋ አማካኝነት የየወቅቱን የማህበሩን እንቅስቃሴ ዘገባ ለሚመለከታቸው ብሄራዊና ዓለም አቀፋዊ የሙያና የአጋር አገልግሎት ድርጅቶች የማሳወቅ እርምጃ ነው። ይህ ተግባር ግልጽ፣ ሊበራልና በብቁ የቅልጥፍና ደረጃ እስካሁን ሰዓት ተካሂዷል። ወደፊትም ይቀጥላል። አማራጭ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ድርጅት የመመስረቱን ተግባር በከፍተኛ ወኔ እና እልህ እያካሄድን ባለንበት በአሁኑ ወቅት ነው ከኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ የተቃዋሚ ፖለቲካ አራማጅ ከሆኑት መካከል በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ሃላፊነት ስር የሚንቀሳቀሰው የግንቦት ሰባት ፓርቲ ስለ "ኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን(ኢሳት)" የእወጃ ፕሮግራም ጅማሬ ያወያዩን።

ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው ሃላፊነት በክንፉ አሰፋ አማካኝነት ሲካሄድ የቆየና ጋዜጠኛውም ስሉጥ እውቅና የስራ ልምድም ያካበተው ከኮሚቴያችን አባላት መካከል እርሱ በመሆኑ "በስደት የሚገኙ የኢነጋማ አባላትን መልዕክት ለኢትዮጵያ ተደራሲዎች የሚያቀብል መገናኛ ብዙሃን እስከሚመቻች ድረስ በሙያችን፣ በዕውቀታችን እና ለሰፊው ህዝብ በገባነው ቃላችን መሰረት" የበኩላችንን አስተዋጽኦ ለማድረግ አቋም ወሰድን።

ክንፉ አሰፋ የሙሉ ጊዜ የዕለት እንጀራ ማግኛ ስራ ስለሚያከናውን በሳምንቱ መጨረሻ ከአርብ እስከ እሁድ በጋዜጠኝነት ሙያ ሊያግዝ፣ የሚሰጠውም አገልግሎት በበጎ ፈቃደኝነት እንጂ በቁሳዊ ክፍያ ላይታጀብ፣ እራሱ በነፃ ህሊናው ወስኖ ለድርጅቱ አስታወቀ።

በሌላ አንፃር ግን ማናችንም አግባብነቱ ከቶውንም የማይታዬን በህብረታዊው አገልግሎት ውስጥ የአንድ ፓርቲ አባላት በህይወታቸው ቆጥረውትም ሆነ አፍርተውት የማያውቁትን ክፍያ በግንቦት ሰባት ድርጅት ዕውቅናና ችሮታ ወጪ እየተደረገ በየወሩ እንደሚከፈላቸው ለማወቅ ቻልን። የክፍያው ጉዳይ ለኢነጋማ አባላት ምንም ባልደነቃቸውና ባልገደዳቸው፤ነገር ግን የብሩን ብዛት የሚመጥን የነፃውን ሚዲያ አሰራር ለአንድ ወገን ጥቅም የሚያስጎብጥ የእዝ ሰንሰለት በጋዜጠኞቹ መካከል በመፈጠሩ የኢነጋማው ወገን በግንባር ቀደም ተቃውሞውን በፊት ለፊት ለማሰማት ተገዷል።

ኢነጋማ አስቀድሞ ያሸተተው የስልጣን ብልግና እና የአንድ የህብረቱ አባል ፓርቲ በሌሎች ኪሳራ እብጠት መጎናጸፍ ወዲያውኑ ማንም ሳይጨመርበት ራሱን በአደባባይ አጋለጠ።

የኢሳት አለቃ ፣ ባለቤትና ፈላጭ ቆራጭ ባለስልጣን በህብረቱ ውስጥ ራሱን የግንቦት ሰባት ተጠሪ አድርጎ የሰዬመ ግለሰብ ነው። ሌሎቹን የህብረቱን አባላት ለራሱ ስልጣን የማስገዛት ተንኮልና ሴራ ሲገምድ የሚውል በአጭር እይታ የታጠረ ግለሰብ ነው። የአንድ ፓርቲ አባልነት ዕይታው ላይ ተመስርቶ በተደጋጋሚ በእኔ በአቶ ከፋለ ማሞ ዓለሜ ላይ የሚቃጣውን ኢ-ዲሞክራሲያዊና አምባገነናዊ አካሄዱን እንደተጠቂነቴ በፊት ለፊት ክርክር ስታገለው ቆይቻለሁ።

በመጨረሻውም አብሮ የመስራቱ ችሎታ ስለተሟጠጠበት ተጠቃሹ ግለሰብ አቶ ፋሲል የኔዓለም ሐሙስ <u>መስከረም 11 ቀን 2006 ዓ.ም</u> እንደ ምስጢር ነጋሪ ለብቻዬ ጠርቶ ወስዶ የሚከተለውን የመሰነባበቻ ቃል ሊነግረኝ ችሏል።

“ድርጅቱ ለአንተ የሚሆን በቂ ገንዘብ ስለሌለው ከዛሬ ጀምሮ የኪስ ገንዘብ አታገኝም።” ሲል ተናግሯል።

ስለሆነም ለኢትዮጵያ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ትግል ዋልታና ማገር ይሆናል ተብሎ የታለመው ይህ የሚዲያ ተቋም የሁላችንንንም ፍላጎት በሚያቅፍ መልኩ ሊተዳደር ባለመቻሉ፣ ከአሰራር ግልጽነት ይልቅ በውዥንብር በመታጠሩ፣ ባለቤት የለሽ እስኪመስል ድረስ ዞሮ ተመልካች በማጣቱ፣ አግባብ ያለው የስልጣን ክፍፍል ባለመኖሩ እንዲሁም በጣት በሚቆጠሩ ግለሰቦች ምክንያት ጋዜጠኞች አላግባብ እየተንገላቱ የእርምት እርምጃ ባለመወሰዱ ከሚከተለው ውሳኔ ላይ ልደርስ ችያለሁ። ነፃ ጋዜጠኝነት አብቦ ተደራሹ ህብረተሰብ ከተጠቃሹ መገናኛ ብዙሃን በአግባቡ መገልገል ባልቻሉበት በዚህ ሁኔታ እኔም ሙያዊ ግዴታና ሃላፊነቴን ለመወጣት መሰናክል ፈጥሮብኛል። በመሆኑም በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሳቢያ ከኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) ራሴን እንዳገለልኩ በዚህ ማስታወሻዬ በድጋሚ አሳውቃለሁ።

Kefale Mammo
Boniplein 25
1094 SC Amsterdam
The Netherlands
Tell: +31 204633480
+31 643081781

* የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበር መስራች፣ ሊቀመንበር እና የኢነጋማ ዓለም አቀፍ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ የኢሳት ተባባሪ አዘጋጅ።